# እንደ አልባራዳይ ብርታቱን ይሰጠን__(ከሎሚ ተራ) 27/09/13

**አድነነ ከመአቱ: ከሻአቢያ እና ከ7ቱ ።** ተመስገን ደሳለኝን አመሰግኜ ነው ዛሬ መጣጥፌን የምጀምረው። ይገርማል የሰሞኑ ሐሳቤና ጭንቀቴ የነበረው በርግጥም ሰለወያኔ ሥረአት ማክተም ሳይሆን፤ ወያኔ ከተወገደ በሖላ ምን አይነት ሰርአት ነው ሊመሰረት የሚችለው ? የሚለው ነበር። በተለይ ከሻአቢያ ጋር የማበር አባዜ ከተነሣ ወዲህ እረፍት አልሰጥ ብሏኛል። ታዲያ ይህንኑ ሳወጣና ሣወርድ አድሬ፤ እንደወትሮዬ ማልጄ ተነስቼ ድሕር ገጾችን ሰመለከት የተመሰገን ደሳለኝን ***"ከለውጡ በሖላሰ ?"*** በሚለው ፅሁፉ እሰካሁን የተወጣበትንና የተወረደበትን የፖሎቲካ ድርጅቶችን እንቅሰቃሴ በቅጡ ከገመገመ በሖላ፤ የወያኔ ውድቀት አይቀሬነቱን አረጋግጦ ከሚመጠው ለውጥ ባሻገር ሊደረጉ የሚገባቸው ናቸው ብሎ ያላቸውን ጠቃሚ ነጥቦቸ ጠቆም ጠቆም አድርጓል ልብ የሚል ልብ ይበል ነው ነገሩ።

እኔም በተመሰገን መጣጥፍ ከሞላጎደል የምሰማማበትና በተለይም በመጨረሻው ሃሳቡ "*እንደ አልባራዳይ*" የሚለውን ለመጋራት ነው። ከሻአቢያ ጋር ሕብረት ከሚለው *"ከመ አቱ ፤ ከ7ቱ"* ሃሣብ መቶ በመቶ የተሻለና የሚደገፍ ነው ብዬ ሰለማምን ነውና የሚሻልበትን ብዙም ሃተታ ሣላበዛ እንደተለመደው በ 2 ሀሳብ ጥንታዊ በሆኑ ተረታዊ አባባሎችን መንደርደሪያ እያደረግኩ ነጥቦቼን ላሰቀምጥ። ምክነያቱም ነገር ቢበዛ በአኽያ አይጫንምና ነው።

ሆኖም አሁንም አንባቢያንን በአክበሮት የምለምነው፤ ያገር ጉዳይ ሆኖ የሻአቢያ ነገር አልዋጥልኽ ብሎኝ እንደዜጋ የዲሞክራሲ መብቴን ተጠቅሜ የሚሰማኝን ሃሳብ ለማካፈል እንጂ፤ ወያኔንን የሚቃወሙና የሚታገሉን ወገኖቼን በምንም አይነት ሁኔታ ማንኛውንም ድርጅትም ሆነ ኢትዬጲያዊ ወገኔን የመቃዎም አባዜ ይዞኝ እንዳልሆነ በትህትና እንድትረዱልኝ አደራ እላለሁ።

## *1ኛ) "አዘለም አቀፈም ያው ተሸከመ ነው:"። እንዲሉ፤-*

ጫካ ገብቶ ለመታገል መወሰንም ሆነ ወደ አገርቤት በመመለሰ የሰላሙን ትግል መቀላቀል የቃላት ልዩነት ካልሆነ በሰተቀር ያው አይመሰላችሁም ? ዋናው ለመሞት መቁረጡ ላይ ነው ። ለምሳሌ ጂ7 በሻአቢያ እርዳታ ወያኔን ለመጣል ምሁራኖችም ጫካ ገብተዋል ? ብለው ሲሉ ያው በግልፅ እንደሚታወቀው ለመሞት ወሰነዋል አፈር ላይ ለመተኛት፤ አፈር ለመብላት ብሎም ወያኒ አሰኪወገድ በቆራጥነት መታገል መሆኑን ማንም ይረዳዋል። ታዲያ ከሻአቢያ ጎን ቆሞ በሕዘብ ልብ ከፈተኛ ሰጋት ከመጣል ? በእወነት ከቆረጡ የሚሊዎኖችን ልብ ከሰጋት በማዳን በሃገር ውሰጥ መሬት ከወያኔ ጋር ፊት ለፊት እንደ ወጣት ታጋዬቹ የሚሊዎኖቹን አገራዊ ድጋፍ እያገኙ መታገል የተሻለ አይሆንም ትላላችሁ ? በርግጥ ተመሰገንም እንደጠቆመው ጂ7 በወያኔ የታገደና የተፈረደበት እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም ቅሉ የተፈረደባቸው እነማን እንደሆኑና ቁጥራቸውም ቢሆን በግልፅ የታወቀ አየመሰላችሁም ሰንት ናቸው ? ብዬ ብጠይቃችሁም እንኳን ወዲያው ትመልሡታላችሁ ግን አልጠይቅም። ዋናው ጥያቄ ደጋፊዎቹ ጋነው ያለው። ወገኖቼ ተመሰገን በመጨረሻው መደምደሚያው ላይ የጠቆመንን ተሳትፎ እንዴት ታዩታላችሁ ? "***እንደ አልባራዳይ***" ትግሉን የመቀላቀሉ ጊዜ አሁን አይመሰላችሁም? እኔ እነደሆነ ቆርጫለሁ። እነዴት ነው የሚገባው ? ተበሎ አይጠየቅም ያው እንዳወጣጣችን ነውና። አቤት ወያኔ ጉድፈላበት ዘንድሮ !!።

## 2ኛ) *"ያልታደለ በሬ ሰጋው ተበልቶ ቆዳው ለከበሮ ይውላል" ። አነዲሉ፤-*

በወያኔ የግፍ አገዛዝ ሕዘባችን ይኸ ነው የማይባል መከራና ሥቃይ ላለፉት 22 አመታት እንደደረሰበትና አሁንም በደሉና አፈናው፣ እሰሩም፤ ግድያውም ሆነ ሰደቱ መልኩን እየቀየረ ሂደቱ በመቀጠል ላይ እንደሆነ ያደባባይ ሚሰጥር ሆኖ ሣለ፤ እንደገና ከቀንደኛ ጠላታችንና ወያኔን ኮትኩቶ አሳድጎ በጫንቃችን ላይ ከጫነብን ሻአቢያ ጋር ወግኖ ከወያኔ ነፃ መውጣት ይቻላል ብሎ ማሰብ በጀግኖቹ ወጣት የሰላም ታጋዬች ተገዝግዞ ቢገፉት ሊወድቅ የተቃረበውን ወያኔን እንደገና እንዲያንሰራራ ያለጥርጥር መርዳት ነው። ይሕ ማለት ደግሞ በወያኔ የግፍ ሥረአት መከራውን የበላውን ሕዝባችንን እንደገና አሳሩን ማብዛት ነውና ካልታደለው በሬ ተረት ሰለማይለይ፤ ይቅርብን አይበጀንም ይቅር ። ይልቅ "***እንደ አልባራዳይ***" በሙሉ ልብ የተጀመረውን እና ሊጠናቀቅ ጥቂት የቀረውን ትግል ወደፍፃሜ እንዲፋጠን በመትመም እንቀላቀል ። አምላክ ይርዳን ። ብርታትና ፅናትም ይሰጠን አሜን ! ።